# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

13

- ★ አዲስ ምዕራፍ
- ★ የዓለም ሕዝቦች አብዮታችንን ይደግፋሉ
- ★ የሶሻል ዲሞክራሲ ሁለት ታክቲኮች
- ★ የካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር

ጥቅምት ፴ — ፲፱፻፸፱ ዓ. ም.

**ለውይይት መነሻ**

አብዮታዊት ኢትዮጵያ ከቍጥር ፩ ጀምራ «ለነማርክስ ፍልስፍና አጭር መግቢያ» በሚል ርእስ ሥር በተከታታይ ትምህርታዊ የሆኑ የፍልስፍና ጽሑፎች ታቀርባለች ። እነዚህ ጽሑፎች የማርክሲዝምን ርእዮተ ዓለም ገና ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚተዋወቁ የውይይት ክበቦች መነሻ ሃሳቦች እንደሚሰጡ ሆነው የቀረቡ ናቸው።

# የካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር

## ፱ኛ ትምህርት ከን - ዓ

የካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር የምርት ኃይሎች እጅግ የዳበሩበት ሥርዓት ሲሆን ጥቂቶች የምርት መሣሪያዎች ባለቤት በመሆናቸው ብቻ ምንም ዓይነት የጕልበት ማሸነፊያ ዘዴ በማውጣት ወዛቸውን ብቻ እየሸጡ ለመኖር የሚገደዱትን ብዙኃን እየበዘበዙ ሀብት የሚያካብቱበት ሥርዓት ነው ።

በዚህ ዘመን በፊውዳል ሥርዓት ውስጥ ነግሠው የነበሩት የባለእጆች ትናንሽ የሥራ ቤቶች በታላላቅ ፋብሪካዎች ተተኩ ። የሳይንስ ምርምር ውጤቶች በኢንዱስትሪ ብቻ ሳይሆን በእርሻም ከሥራ ላይ በሰፊው ይውሉ ጀመር ። በእንፋሎት ኃይል መርከቦች መንቀሳቀስ ጀመሩ ። የባቡር ሐዲዶች ከአገር አገር እያቋራረጡ አህጉሮች አለበሱ ። ኤሌክትሪክ ቴሌግራፍ ፤ ቴሌፎን ዓለምን አቀራረቡ ። ቀደም ሲል ያልተደፈሩ አህጉሮች እንዳሉ መመንጠርና ለማዕድናቸው ሲባል እየጠለቁ መቦርቦር ጀመሩ ። ወንዞችና ጅረቶች ተገድበው የኢንዱስትሪ እንቀሳቃሽ ኃይል ሆኑ ። ከተሞች በያለበት እየተቀረቀሩ አንሰራሩ ፤ ባጭሩ ጠቅላላውን የሰው ዘር በካፒታሊስት ቀደም ሥርዓቶች በሙሉ ከተራመደው ይልቅ በካፒታሊዝም ሁለት መቶ ዓመታት ድርብ ድርብ ርብ እርምጃ አደረገ ።

ይህ ሁሉ እድገት የተገኘው የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነት እንዴት ተቀነባብረው ነው። በመጀመሪያ ልብ ማለት ያለብን ሁለት ነገሮች አሉ ። አንደኛ የካፒታሊስት ሥርዓት ከባሪያና ከፊውዳል ሥርዓት የሚሻለው በምርት ኃይሎች መዳበርና በውጤታቸው ጥራት እንጂ በካፒታሊዝም ውስጥ ያሉት የምርት ግንኙነቶች ያው እንደሁለቱ በብዝበዛ ላይ የተመሠረቱ ናቸው ። ሁለተኛ ደግሞ ይህንን ሥርዓት ሌላ ዓይነተኛ የሚያደርገው እንደቀደሙት ሥርዓቶች ዓይን ያወጣ ብዝበዛና ጭቆና ሳይሆን የተሸፋፈነ ፤ የሚበዘብዝና የሚጨቁን የማይመስል ፤ እንዲያውም ይህንን ሁሉ ጨርሶ የሚክድ ሥርዓት ነው ። እውነትም ደግሞ ጠጋ ብሎ ላል ተመለከተ ካፒታሊዝም ብዝበዛ የሌለበት ፤ እኩልነት ነፃነትና ወንድማማችነት የሰፈነበት ሥርዓት ሊመስል ይችላል ። ስለዚህ ይህ እንደቀደሙት ሥርዓታት በብዝበዛ ላይ የቆመ ሥርዓት እንዴት እንደሚበዘብዝ እስቲ ጠጋ ብለን እንመልከት ።

የካፒታሊስት ሥርዓትን ዓይነተኛ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ የምርት ሥራ ሁሉ የሚያተኩረው ሸቀጥን ለማምረት መሆኑ ነው ። ይህ ምን ማለት ነው ? ይህም ማለት ማንኛውም ሰው በተወሰነ መስክ ተሰማርቶ የሚሠራው በዚያ በሠለጠነበት መስክ ምርቱን ከፍ አድርጎ ገበያ ለማውጣትና እሱን ለመሸጥ እንዲችል ነው ። በዚህ እንግዲህ የምርት ግንኙነቶች በብዝበዛ ላይ የተመሠረቱ በመሆናቸው የመሣሪያዎች ባለቤት የሆነው ካፒታሊስት የጠቅላላው ምርት ባለቤት ነው ። ክፍያ በሚደረግበት ጊዜም ለእሱ አንቀባሮ የሚያኖረውን ብቻ ሳይሆን ሥራውንም ለማስፋፊያ የሚሆነውን ሀብት ይወስዳል ። ለወዝአደሩ ደግሞ እሱና ቤተሰቡ በረኀብ እንዳያልቁ በኑሮ ጠርዝ ላይ አንጠልጥላ የምትይዘው ደመወዝ ብቻ ይከፈለዋል ።

ካፒታሊስቱ በዚህ ክፍያ እኔም የካፒታሉን ዋጋና የልፋቱን ወሰድሁ ፤ ለወዝአደሩም የልፋቱን የሥራውን ዋጋ ከፈልኩ የት ላይ ነው የዘረፍኩት ብሎ ለማወናበድ ይሞክራል ። ታዲያ የብዝበዛው «ምሥጢር» የት ላይ ነው ?

በመሠረቱ ሁሉ የሚሸጥ የሚለወጥ በሆነበት በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ የሰው ጉል

በትም ራሱ እንደሸቀጥ ገበያ ወጥቶ የሚሸጥ የሚገዛ ነገር ነው ። ከላይ እንዳየነው ለከበርቴ ሥርዓት መስፋፋት ከባላባት ቍጥጥር ነፃ ሆኖና፤ በሀብት በኩል ደግሞ ጨርሶ ሙልጨን ወጥቶ በወዙ ብቻ ለመተዳደር የሚገደድ ሰው በብዛት አስፈላጊ ነው ። በዚህ መልክ መተዳደሪያ በማጣት ወደከበርቴው ለመቀጠር የሚሔደው ወዝአደር የሥራ ጉልበቱን ለመሸጥ ይቀርባል ። የሥራ ጉልበቱ ስንት ያወጣል? የሰው ጉልበት ዋጋ የሚወሰነው ያንን ጉልበት ለማቅረብ ያስፈለጉት ነገሮች ሁሉ ተደምረው ነው ። የሥራ ጉልበቱን ለማቅረብ ወዝአደሩ መብላት ፤ መጠጣት ፤ መልበስ መጠለል . . . አለበት ። የሥራ ጉልበት ያለማቋረጥ እየታደሰ ሲያረጅ የሚተኩትን ልጆች መውለድና ማሳደግ አለበትና ለቤተሰቡም አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች በዚሁ መልክ ለማቅረብ መቻል አለበት ።

ባጭሩ የጉልበት ዋጋ የሚወሰነው ለወዝ አደሩና ለቤተሰቡ በሕይወት መኖርና መሥራት መቻል አስፈላጊ በሆነው ክፍያ ነው ። ይህ የሥራ ጉልበት በገበያ የሚሸጥበት ዋጋ ሲሆን በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ደመወዝ እየተባለ ይከፈላል።

እንግዲህ ከበርቴው ወዝአደሩን የሚከፍለው ለሠራው አይደለም የሥራ ጉልበቱን ለመግዛት እንጂ ። ይህ ነገር ቀላል ይመስላል ። ግን የካፒታሊዝም ብዝበዛ «ምሥጢር » ያለው እዚህ ላይ ነው ።

ከበርቴው ወዝአደሩን በሚቀጥርበት ጊዜ ስምምነታቸው ያኛው የጉልበቱን ዋጋ (ማለት ደመወዙን) ሊሰጥ ይኸኛው ደግሞ ጉልበቱን በቀን ለተወሰነ ሰዓት ሊሸጥ ነው ። ወዝአደሩ ተቀጥሮ በቀረበለት መሣሪያ እየተረዳ ፤ ጥሬውን ዕቃ በሚፈልገው መልክ ሠርቶ ለገበያ ያቀርባል ። የዚህ ሸቀጥ ዋጋ እርግጥ የወዝአደሩ ጉልበት ብቻ አይደለም ። ጥሬ ዕቃው ፤ መኪናው ፤ ቤቱ ፤ ይጨመርበታል ።

ለምሳሌ እስቲ አንድ ከበርቴ 200 ሚማዎች አሠርቶ ገበያ ሲያወጣ እንከተለው ፦

| | |
|---|---|
| 200 ሚማ ለማሠራት ቆዳና ሌላ ጥሬ ዕቃ | = $ 2000 |
| የመኪና ፍጆት . . . . . . . . | = $ 250 |
| 50 ወዝአደሮች በ$ 3.00 ሂሳብ በቀን . . | = $ 150 |
| ጠቅላላ ወጪ . . . . . . . . | = $ 2400 |

እንግዲህ እነዚህን ሚማዎች ፤ ለማሠራት እያንዳንዱ ሚማ $ 12 ፈጅቷል ማለት ነው ። ከበርቴው እንኳን ትርፍ ትንሽ ጨምሮበት ይቅርና እያንዳንዱን ሚማ በዚህ በ$ 12 እንኳን ቢሸጥ በዝብዞ ትርፍ ያካብታል ። እንዴት ?

ምክንያቱም እንኳን በተራቀቁ መሣሪያዎች ይቅርና በጣም ወደኋላ በቀሩ መሣሪያዎችም ቢሆን ከጋርዮሽ ሥርዓት ወዲህ የምርት መሣሪያዎች አድገዋልና ማንም ሰው ቢሆን በቀን ለተወሰነ ጊዜ ከሠራ «ለኑሮ ያስፈልገዋል » የሚባለውን ሀብት ሊያፈራ ይችላል ። በተለይ ደግሞ እንደ ካፒታሊዝም ዓይነት የተራቀቁ መሣሪያዎችና የሥራ ዘዴዎች ያሉት ሥርዓት ውስጥ «ለዕለት እንጀራ» ብቻ ከሆነ አንድ ሰው በጣም ትንሽ ጊዜ ቢሠራ ይህንን ከበርቴው ደመወዝ እያለ የሚከፈለውን «ለኑሮ የሚያስፈልገውን » ሀብት ያገኛል ። ነገር ግን ወዝአደሩ ይህንን በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ማምረት ቢችልም ጉልበቱን ለከበርቴው የሚሸጠው በቀን ቢያንስ ፪ ሰዓት ለመሥራት ነው ። እንግዲህ ትርፉ የሚመጣው እዚህ ላይ ነው። ከላይ ያየነውን ምሳሌ እንደገና እንውሰደው ።

ወዝአደሮቹ በፋብሪካ ውስጥ ሲሠሩ « ለኑሮ አስፈላጊ » የተባለውን ደመወዝ በቀን ፰ ሰዓት ቢሠሩ ይደርሱበታል እንበል ። የሚከፈላቸው ከዚህ ባይነቃነቅም በቀን ፪ ሰዓት ስለሚሠሩ ከበርቴው የገዛው የሥራ ጉልበት ፬ እጥፍ ይሆናል ማለት ነው ። ስለዚህ የወዝአደሮቹ ደመወዝ ከዚያው ሳይነቃነቅ በቀን የሚሠራው ሚማ ብዛት ፬ እጥፍ ይሆናል ። ማለት ነው ።

| | |
|---|---|
| 4 × 200 ሚማ ለመሥራት ቆዳና ጥሬ ዕቃ | =$ 8000 |
| » » » የመኪና ፍጆት | =$ 1000 |
| 50 ወዝአደሮች በ$ 3 ሂሳብ ለቀን | =$ 150 |
| ድምር . . . | =$ 9150 |

አሁንም ከበርቴው በለመደው በ$12 ቢሸጥ $ 9600—9150=$ 450 ንጹሕ ትርፍ ያገኛል ማለት ነው ። ይህ ልዩነት የጥሬ ዕቃውን ዋጋ ፤ የመኪናውም ፍጆት ገብቶ ሲታሰብበት የወዝአደሩ ጉልበት ግን እንዳልነበረ የተቆጠረበት በመሆኑ የተገኘው ወዝአደሩን በመበዝበዝ ነው ማለት ነው ።





ለካፒታሊዝም የሕይወት እስትንፋስ የምትሰጠው የሕይወቱ ተስፋና አለኝታ ፤ እንግዲህ ወዝአደሩ በዚህ መልክ ከሚከፈለው በላይ እየሠራ የሚያፈራውና ለከበርቴ የሚያስረክበው ምርት ሲሆን ይህንን ሀቅ ፈልፍሎ ያገኘው ካርል ማርክስ «ትርፍ ምርት » ወይም « ሰርፐለስ ቫልዩ» ብሎ ሰይሞታል ።

ከበርቴው የሚወጣና የሚወርደው ትርፍ ምርቱን ለማሳደግ ነው ። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ወይ የሥራን ሰዓት ማራዘም ወይም ደግሞ ወዝአደሩ በኀብረቱ አይሎ ካስቸገረ መኪናውን የተራቀቀ በማድረግ ደመወዝተኛውን በመቀነስ ነው ።

በየትኛውም መንገድ ብንሄድ የከበርቴው የማያቋርጥ ጥረት «ለኑሮ አስፈላጊ» የሚባለውን ደመወዝ መብላት ፤ መጠጣት ፤ መጠለልን ከመሰለው ጋር ብቻ አያይዞ በተቻለ ዝቅተኛ ለመክፈል ነው ። ወዝአደሩ ደግሞ «ለኑሮውም ያስፈልገኛል» የሚለው ከመብላት ከመጠጣት አልፎ በላቡ ከሚያፈራው ሀብት ተስተካካይ የሆነ ድርሻ አግኝቶ የተሟላና እየተሟላ የሚሄድ ኑሮ ለመኖር ነው የወዝአደሩ ድርሻ እንዲጨምር ከተፈለገ የከበርቴው ድርሻ መቀነስ ይኖርበታል ። እንግዲህ በመሠረቱ የወዝአደሩና የከበርቴው ፈጽሞ የማይጣጣምና ተፃራሪ የጥቅም ግጭት እዚህ ላይ ነው ።

በተጨማሪ ደግሞ ወዝአደሩ የሥራ ዋጋውን በሚገባ አለመከፈሉ የካፒታሊዝምን ኢኮኖሚ በየጊዜው ከፍተኛ ቀውስ (ክሪዝ) ውስጥ እየጨመረ ሲያንገዳግደው እናያለን ። ይህ ክሪዝ ከ፲፱ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በካፒታሊስት አገሮች እየተደጋገመ የታየ ክሪዝ ነው ። የከበርቴ ኢኮኖሚስቶች ይህንን ከረኃብ ሳይሆን ከቁንጣን የመጣ ችግር ለማስመሰል «ከሚገባ በላይ በማምረት» የመጣ ችግር ብለው ያቀርቡታል ።

እውነትም ላይ ላዩን ለተመለከተ ሰው ይህ ካፒታሊዝምን የማይለየው አልፎ አልፎ የሚደጋገም ቀውስ ከምርት መትረፍረፍ የፈለቀ ይመስላል ። ምክንያቱም በእንዲህ ዓይነቱ ጊዜ ሸቀጥ ተትረፍርፎ ይታያል ። ነገር ግን ሰፊው ሕዝብ በልቶ ፤ ጠጥቶ ፤ ለብሶ ፤ ለኑሮ የሚያስፈልገውን ሁሉ አግኝቶ ነው» ከሚያስፈልገው በላይ ተመረተ የሚባለው? አይደለም ። የሚሰጠው ደመወዝ በሚሠራው ልክ ቢሆን ኖሮ ይህንን ዕቃ ገዝቶ ሊጠቀም ይችል ነበር ። ነገር ግን ወዝአደሩ የሠራው ሁሉ ራሱ ሊገዛ የሚችልበት ገቢ ከተከፈለው ከበርቴው በምን ዘዴ ትርፍ ያካብት? ይህን ካደረገ «ወይኖ አረሰው ወይኖ ጐረሰው» የተባለው ተረት ይሆናል ። ስለዚህ ገበያ የቀረበውን ዕቃ ወዝአደሩ ሊገዛ እንዲችል የወዝአደሩን ደመወዝ መጨመር ለካፒታሊስቱ አደጋች ነው ። ግን ደግሞ የወዝአደሩ ገቢ በኑሮ ጠርዝ ላይ የምታቆመው አነስተኛ ደመወዝ እስከሆነች ድረስ ዕቃውን ሊገዛ አይችልም ።

ስለዚህ ይህ ዓይነቱ ችግር ካፒታሊዝምን ሁልጊዜ የሚከተለው ችግር ነው ። በዚህም ወቅት ከበርቴዎች ዕቃ በዝቶብን ተትረፈረፈን ተቸገርን ይበሉ እንጂ በሌላ በኩል ደግሞ ሠራተኛ ስለሚያባርሩ ወዝ አደሩና ቤተሰቡ እንዲያውም በሥራ አጥነት የሚገረፍበትና የሚቀምሱት እያጡ የሚሠቃዩበት ወቅት ነው ።

በመሠረቱ ይህና ሌላም ከላይ የጠቀስነው የካፒታሊስት ሥርዓት ግጭት የሚፈጠረው ከምርት ግንኙነቶች ከቀን ቀን እየተዛቡ መሄድ እንደሆነ ግልጽ ነው ። በምርት ኃይሎች ማደግ የተነሣ የምርት ሥራ ከቀን ቀን የኀብረትና የትብብር የመተጋገዝ እየሆነ ይሔዳል ። ነገር ግን በሺህና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ተጋግዘውና ተባብረው በየፋብሪካው የሚያፈሩት ሀብት በመቶ በማይቆጠሩ ከበርቴዎች ከቀን ቀን እየኀላ በመሔዱ በወዝአደሩና በከበርቴው መሀከል ያለው ትግል እየተፋፋመ ይሔዳል ።

ቅራኔው ሊፈታ የሚቻለው ሰዎች በኅብረት ለጋራ ጥቅም የሚሠሩበት ኅብረተሰብ ሲመሠረት ብቻ ነው ። ይህ ደግሞ የምርት ግንኙነቶችን የምርት ኃይሎች በደረሱበት ደረጃ ተስማሚ በሆነ መልክ በመለወጥ በእርግጥ ብዝበዛ የሌለበትና በእኩልነት ሊሠራ የሚቻልበት የምርት መሣሪያዎች የጥቂት ሰዎች ሳይሆን የጋራ የሆኑበት የሶሻሊስት ኅብረተሰብ ሲፈጠር ነው ።